# የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

# የትራንስፖርት አጠቃቀም እና አስተዳደር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 449/2013

**ጥር 8/2012 ዓ.ም**

## 1. መግቢያ

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ከተለያዩ ሀገሮች ጥባና ከለላ ፈልገው ወደ ሀገራችን ለሚገቡ ስደተኞች መሰረታዊ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች እንደሚሰጥ ይታወቃል፣ ከሚገኘው ድጋፍ ውስጥ አንዱ ተሽከርካሪ ሲሆን እነዚህን ውስን ሀብት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ ማዋል እንዲቻል በትራንስፖርት አጠ ቃቀምና አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመፈተሽ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር በማበጀት የትራንስፖርት እና ጥገና አገልግሎትን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ምቾ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለምፈት ለመስጠት ከዚህ በፊት የነበረውን አሰራር ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም፡-

- ❖ ኤጀንሲዉ በእርዳታ እና በግዥ የሚያገኛቸውን ተሽከርካሪዎች በአግባቡ ለማስተዳደር፣
- ❖ ለመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚያስፈልገውን ነዳጅና የተለያዩ መለዋወጫዎች አቅርቦት ለማሟላት እና አጠ ቃቀማቸውን ለመቆጣጠር፣
- ❖ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የመከላከልና ከፍተኛ የጥገና አገልግሎት በብቃትና በተገቢው ጊዜ ተከታትሎ በመፈፀም ረጅም እድሜ እንዲያገለግል ለማስቻል፣
- ❖ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች አስተማማኝ የመድን ዋስትና የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣
- ❖ ከመ/ቤቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ለሰራተኞች ተገቢውን የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት፣
- ❖ መ/ቤቱ የሚያጋጥሙትን የኢመርጀንሲ ሥራዎች በብቃት ለመወጣት እንዲቻል፣

ኤጀንሲዉ ከዝህ ቀደም የነበረዉን መመሪያ በመከለስ ይህንን የትራንስፖርት አጠቃቀም እና ጥገና አስተዳደር መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ የትራንስፖርት እና ጥገና አስተዳደር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 449/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ት ር ጓ ሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡፡

1. «ኤጀንሲ ወይም መ/ቤቱ» ማለት የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ነው፡፡
2. «የበላይ ኃላፊ» ወይም ከፍተኛ አመራር ማለት የኤጀንሲዉ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል እና ም/ዋና ዳይሬክተር ጀነራል ናቸው፡፡
3. መካከለኛ አመራር ማለት የዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች፣ የፅህፈት ቤት ኃላፊ፤ የአገልግሎት ኃላፊ እና ማለት ነው፡፡
4. ዝቅተኛ አመራር ማለት የማስተባበሪያ ጽ/ቤት አስተባባሪዎች፤ የመጠለያ ጣቢያ አስተባባሪዎች፤ የማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማኔጅመንት፤የመጠለያ ጣቢያ ማኔጅመንት፤የቡድን መሪዎች፣ ማኔጅመንት አባላትና በዚህ ደረጃ ተመድበው የሚሰሩ ማለት ነው፡፡
5. ሰራተኛ ማለት ከፍተኛ ኦፊሰሮች እና ከዚያ በታች ያሉ ሁሉም የኤጀንሲው ቋሚ ሰራተኞች እና ግዜያዊ ሰራተኞች ማለት ነው፡፡
6. «ተሽከርካሪ» ማለት የኤጀንሰዉ ንብረት የሆኑ ወይም በትውስት ለጊዜው የመጡ ቀላል እና ከባድ ባለ አራት እግር፣ ባለ ሶስት እግር፣ ሞተር ሳይክል እና ሌሎች ለየ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፡፡
7. ኤክሰስ/Excess/ ማለት የመድን ሽፋን መነሻ ዋጋ ማለት ነዉ፡፡
8. በዝህ መመሪያ ዉስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸዉ የትራንስፖርት አጠቃቀም ቃላት በመድን ድርጅቶች የሚሰጣቸዉን ትርጉሞች ይይዛሉ፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የትራንስፖርት አጠቃቀምና እና አስተዳደር አፈፃፀም መመሪያ በስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ተግባርና ሃላፊነት ጋር ተያያዥነተባላቸዉ ተግባራት የተሠማራ አመራርና ሠራተኞች እና ሌሎች አካላት ውስጥ ባሉ ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የተሽከርካሪ ምደባና አገልግሎት አሰጣጥ</u>

## 2. የተሽከርካሪዎች ምደባ

2.1.ኤጀንሲዉ ለመ/ቤቱ ዳይሬክተር፣ ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ ለዳይሬክተሮች፤ ለአገልግሎት ኃላፊዎች፣ ለጽ/ቤት ኃላፊ፤ ለቡድን መሪዎች ለትራንስፖርት ኦፊሰር እና ለዞን አስተባባሪዎች ተሽከርካሪ ይመድባል፡፡እንድሁም በሥራ ፀባያቸው ምክንያት መኪና በግል እንዲይዙ በከፍተኛ አመራር ለሚፈቀድላቸው ሌሎች ሠራተኞች ተሽከርካሪ ይመድባል፡፡

2.2.ከዝህ በላይ ባለዉ ንኡስ አንቀጽ 2.1.በተገለጸዉ መሰረት ተሽከርካሪ የተመደበለት አካል ለተሽከርካሪዉ የሚያስፈልገዉ ነዳጅ በጥቅማ ጥቅም መመሪያ መሰረት ይሰጠዋል፡፡

2.3 ኤጀንሲዉ በንኡስ አንቀጽ 2.1. መሰረት ይመደብለት የነበረ ነገር ግን ተሽከርካሪ ባልሰጠዉ አካል ተሽከርካሪ በግል የሚያቀርብ ከሆነ በከፍተኛ አመራር ዉሳኔ ነዳጅ ሊሰጠዉ ይችላል፡፡

2.4.ኤጀንሲዉ ለዞኖችና ለካምፖች የተሽከርካሪዎች ምደባ የሚያካሂደው በሚኖረው የሥራ ባህሪ፣ የመንገድ ዓይነት፣ የተሽከርካሪው አገልግሎት አይነት የሥራ ቦታ እና የሥራው አጣዳፊነት መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

2.5.በሥራ ፀባያቸው ምክንያት የሰርቪስ አገልግሎት ወይም በግል ተሽከርካሪ /ሞተር ሳይክል መመደብ ሲገባ በአቅም ማነስ የተነሳ ባልተመደበላቸው በማዕከል ለሚገኙ ሠራተኞች የንብረት አስተዳደር ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ሰራተኛው የሚያወጣውን የትራንስፖርት ወጪ ያገናዘበ የትራንስፖርት ሂሳብ እንዲከፈላቸው እያስጠና ለኤጀንሲዉ ከፍተኛ አመራር በማቅረብ ሲወሰን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2.6ለኤጀንሲዉ ሠራተኞች ከሚኖረበት አዲስ አበባ ከተማ አካባቢ እና በዙሪያዋ የትራንስፖርት አቅም በማገናዘብ በማኔጀመንት በንብረት አስተዳደሩና ጠቅላላ አገልግሎት አቅራቢነት በማኔጅሜንት እየተወሰነ ወደ ስራ ቦታ ሰርቪስ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

2.7ለኤጀንሲዉ ሠራተኞች ሰርቪስ ተሽከርካሪ በጥገና እና በተለያዩ ችግሮች ማቅረብ ካልተቻለ ሠራተኞች የመኖሪያ አካባቢ ርቀት እየታየ የታክሲ ወጪ ይሸፈናል፡፡

## 3. ልዩ ልዩ አገልግሎት አሰጣጥ

3.1. መ/ቤቱ የሚያጋጥመውን የኢመርጀንሲ ስራዎች /ከሥራ ሰዓት ውጪ፣ በበዓላት ቀን፣ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ /በብቃት ለማከናወን የትራንስፖርት ክፍል ሹፌሮችንና መኪናዎችን /አምቡላንስን ጨምሮ/ በኘሮግራም የሚመድብ ሲሆን ከስራ ሰዓት ውጪ አሽከርካሪውን በትርፍ ሰዓታቸው ላገለገሉበት በኤጀንሲዉ የጥቅማ ጥቅም መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

3.2. ለኤጀንሲዉ ሥራ ከዞንና ከላምኘ ወደ ዋና መ/ቤት የሚመጡ ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች የሥራ ሁኔታው እየታየ ሲመጡ እና ሲሄዱ ተሽከርካሪ /መኪና/ ሊመደብላቸው ይችላል፤ ወይም የትራንስፖርት ወጪ ይሸፈናል፡፡

3.3. ለከፍተኛ ህክምና ወደ አዲስ አበባ ሪፈር ለሚመጡ ሠራተኞች ያሉበት ጤና ሁኔታ በግል ትራንስፖርት መጠ ቀም የማይችሉበት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑን በሀኪም ሲረጋገጥ የትራንስፖርት አገልግሎት /አምቡላንስ/ ወይም ሌላ ተሽከርካሪ ሊመደብላቸው ይችላል፡፡

3.4. ለስራ ጉዳዩ በአውሮኘላን ወደ ማዕከል የሚመጡ ሠራተኞችን ከአየር መንገድ እስከ ማረፊያ ቦታቸው፣ ቢሮና ሌሎች በስራ ምክንያት ወደሚሄዱበት ድረስ የትራንስፖርት አገልግሎት በመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ወይም መ/ቤቱ ውል በተፈራረማቸው የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች እንዲጠቀሙ ይደረጋል፤ ወይም በሚያቀርቡት ደረሰኝ መሠረት ያወጡት ወጪ ይሸፈናል፡፡

3.5. በሹፌሮች እጥረት ምክንያት ለአስቸኳይ ለአስፈላጊ ሥራ ጉዳይ በሌላ ሠራተኛ ተሽከርካሪ እንዲያሽከረክር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ሲፈቅድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የአሽከርካሪዎች ሥልጠና እና የመንገድ ሥነ ስርዓት ስለማክበር

### 4. ሥልጠና

- አዳዲስ ሞዴል ተሽከርካሪዎች ለድርጅቱ ሲመደቡ ሹፌሮች እና የቴክኒክ ባለሙያዎች ሥራቸውን በተሳካ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ለማስቻል ኤጀንሲዉ በራሱ ባለሙያዎች ወይም በውጪ የማሰልጠኛ ማዕከላት ለሹፌሮች ተጨማሪ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ይሰጣል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ፣ ደህንነት አጠባበቅ እና አጠቃቀም

### 5. ስለተሽከርካሪ መረጃ አያያዝ

**የትራንስፖርት ክፍል እና ቴክኒክ ክፍል**

5.1. በኤጀንሲዉ ስር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በየወሩ የተጓዙበትን የኪሎሜትር መጠን፣ የተጠቀሙበትን የነዳጅ መጠንና ያሉበትን ደረጃ እየለዩ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መዝገብ ላይ ትራንስፖርት መዝግቦ ይይዛል፡፡

5.2. ጥገና የተደረገላቸው ተሽከርካሪዎች ሲኖሩ የተደረገላቸው የጥገና ዓይነትና ለጥገናው የወጣውን ወጪ በማካተት ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ የቴክኒክ ክፍሉ መዝግቦ ይይዛል፡፡

5.3. ለቀላል ተሽከርካሪዎች 300 ኪ.ሜ እና ከባድ ተሽከርካሪዎች 500 ኪ.ሐሜ የሰርቪስ ጊዜያቸው ከመድረሱ በፊት የጥገና ወረፋ /ተራ/ እንዲያዝላቸው ለቴክኒክ ክፍሉ በተዘጋጀው ቅጽ በመሙላት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

### 6. የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

**የትራንስፖርት እና ጥገና ቡድን**

6.1. አሽከርካሪው የጎማና የውስጥ ላስቲክ /Inner tube/ እንዲሰጠው የሚያቀርበውን ጥያቄ በሙያተኛ ተገቢ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ የተጠየቀው ጎማ ወጪ ሆኖ እንዲሰጠው የንብረት ወጪ ማድረጊያ ቅፅ ይሞላል፡፡

6.2. በንዑስ አንቀፅ 8.6 መሰረት ከመፈፀሙ በኋላ ያገለገለው እቃ ወደ ንብረት  ክፍል መመለሱን ይከታተላል፡፡

፮.፫. ሹፌሮች ለሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ ሲያስፈልጋቸው ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ሞልተው ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ ትራንስፖርትና ጥገና ቡድን ትክክለኛነቱን አረጋግጦ ይፈቅዳል፤

፮.፬. ለስራ ወደ መስክ የሚሄዱ ሠራተኞች እንደሚሄዱበት አካባቢ በቂ የነዳጅ መግዣ በኩፖን ወይም በገንዘብ እንዲሰጣቸው እንዲሁም የሚሰጣቸው የኩፖን ዓይነት ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች በስራ ቦታ የሚገኝ መሆኑን የትራንስፖርት ክፍል ያረጋግጣል፤

፮.፭. የትራንስፖርትና ጥገና ኦፊሰር ነዳጅ በተቀዳ ቀጥር ኪሎሜትረንና የተቀዳውን ነዳጅ መጠን መዝግቦ ይይዛል፣ ወረ ሲያልቅ መኪናው የተጓዘውን ጠቅላላ ኪሎሜትርና የተሞላውን ነዳጅ በመደመር አጠቃቀሙን በማስላት ያመሳክራል፣ ሪፖርት ለቡድኑ ያቀርባል፤

፮.፮. አሽከርካሪው ለሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ ዘይትና ቅባት ሲያስፈልገው እንደአስፈላጊነቱ በቴክኒክ ክፍል ተረጋግጦ የትራንስፖርትና ጥገና ቡድን መሪ/ ኦፊሰር ይፈቅዳል፡፡

፮.፯. የተቋሙን ተሽከርካሪዎች ደረጃ የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ ያደራጃል፡፡

## ክፍል ሰምስት

## የቴክኒክ ምርመራ፣ የተሽከርካሪ አደጋ ሪፖርት ስለማቅረብ እና ጥገና

### ፯. የቴክኒክ ምርመራ ስለማድረግ

የትራንስፖርትና ጥገና አገልግሎት ቡድን

፯.፩. የመ/ቤቱን ከባድ፣ መካከለኛና አነስተኛ ተሽከርካሪዎች በየዓመቱ ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፤

፯.፪. በግዥም ሆነ በእርዳታ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ደብተር እንዲወጣላቸው በማድረግ ኦሪጅናሉ በዋናው መ/ቤት ንብረት ክፍል እንዲሁም ፎቶ ኮፒው ተሽካሪካርዉ በሚገኝበት በማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንዲቀመጥ ያደርጋል፤

፯.፫. የሔጀንሲዉ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የመድህን ሽፋን እንዲያገኙ ያደርጋል እንዲሁም የሶስተኛ ወገን እስቲከር ጊዜውን በመከታተል ለመድን ተረክቦ ተሽከርካሪዎች ላይ በወቀቱ እንዲለጠፍ ያደርጋል፡፡

### ፰. የተሽከርካሪ አደጋ ሪፖርት አቀራረብ

የትራንስፖርትና ጥገና ቡድን

8.1. የአስተዳደር ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ወይም በማ/ጽ/ቤቶች ወይም በመ/ጣቢያዎች ውስጥ አደጋ አደረሰ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ የትራፊክ ፖሊስ እንዲያውቀው ያደርጋል እንዲሁም ለመድን ድርጅት በማሳወቅ የአደጋ ማሳወቂያ ቅፅ በመሙላት ለኢንሹራንስ ያስተላልፋል፤

8.2. አደጋ በደረሰበት አካባቢ የሚገኝ የመ/ቤቱ የሥራ ክፍል ከዚህ በታች የተመለከቱት መረጃዎች ተሟልተው ለኢንሹራንስ መተላለፋን ክትትል ያደርጋል፤

- የፖሊስ ሪፖርት መጠየቅና ማስተላለፍ፣
- የአሽከርካሪ የጽሑፍ ሪፖርት፣ የምስክሮች ሪፖርት፣ የፖሊስ ስምና አድራሻ፣
- የአሽከርካሪ መንጃ ፍቃድ ፎቶ ኮፒ፣
- የደረሰው አደጋ መጠን፣
- የህክምና ወጪ
- በሐኪም የተሰጠ የሞት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፤
- የካሳ ስምምነት ሰነድ፣
- ሌሎች ጠቃሚ ሰነዶች በአባሪነት መያያዝ ይኖርባቸዋል፤

8.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.1 እና 9.2 የመ/ቤቱ ተሽከርካሪ በሌላ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ምክንያት በሰው ህይወት ላይ የሞት ወይም የአካል መጉደል  ወይም እግረኛ ላይ አደጋ አድርሶ ጉዳዩ በፍ/ቤት ታይቶ ወይም በስምምነት በሽምግልና መፍትሄ አግኝቶ በመ/ቤቱ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ካስከተለ፡-

9.3.1.በፍ/ቤት ዉሳኔ ወይም በስምምነት በሽምግልና እንዲከፈል የተበየነው ገንዘብ የኢንሹራንስ ድርጅት የሚሸፍነው የሶስተኛ ወገን ሽፋን ሆኖ ከተገኘ በዚያው በኩል እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

9.3.2. በፍ/ቤት ዉሳኔ ወይም በስምምነት በሽምግልና እንዲከፈል የተበየነው ገንዘብ የአንሹራንስ ድርጅት ከሚሸፍነው የሶስተኛ ወገን ሽፋን በላይ ሆኖ ከተገኘ የአንሹራንስ ድርጅቱ የሚከፍለው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩነቱን በሚመለከት መ/ቤቱ እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

## 9. **የተሽከርካሪው ጥገና**

9.1. አስተዳደሩ የመከላከል ጥገናዎችን እና ቀላል ጥገናዎችን በካምፖችና በዞኖች ባቋቋማቸው ጋራዦች ያካሄዳል፤

9.2. የጥገና ክፍል ኃላፊ ለጥገና የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና መለዋወጫዎችን በማጥናት እንዲሟሉለት ለትራንስፖርትና ጥገና ቡድን ጥያቄ ያቀርባል፤

9.3. በኤጀንሲዉ ተሽከርካሪዎች ጥገና የሚከናወነው በአስመጪ ኩባንያ ጋራዦች፣ በየደረጃዉ ባሉ የኤጀንሲዉ ጋራዦች እና መ/ቤቱ ውል ከተዋዋላቸው ጋራዦች ጥገና ይደረጋል፤ የተከናወኑ ጥገናዎች ትክክለኛነት በቴክኒክ ክፍል ሲረጋገጥ ክፍያው እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

9.4. ጥገና ክፍል ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የአገልግሎት መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚከናወነውን ጥገና አይነት በመዘርዘር ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ፎርም ላይ ለትራንስፖትና ጥገና ቡድን ለያቀርብ እና በንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክተር ሲፀድቅ ትራንስፖትና ጥገና ኦፊሰር በጥገና ማዘጋጃ ቅጽ በመሙላት በአንቀጽ 11.3 ላይ ወደተገለፁት ጋራዦች ይልካል፤

9.5. የትራንስፖርትና ጥገና ቡድን ከባድ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ተሽከርካሪዎች ከካምፖችና ከዞኖች ወደ አዲስ አበባ ዋናው መ/ቤት በማስመጣት በአንቀጽ 12.3 በተገለፁት ጋራዥ ውስጥ እንዲጠገኑ ያደርጋል፤

9.6. የጥገና ክፍል ለጥገና የገቡ ተሽከርካሪዎችን የጥገና ሁኔታ በመከታተል እና በማረጋገጥ ጥገናቸው ሲጠናቀቅ ለትራንስፖርትና ጥገና ኦፊሰር በማስረከብ ወደ ስራ እንዲሰማሩ ያደርጋል፤

9.7. ተሽከርካሪዎች ወደ መስክ ሲጓዙ በመንገድ ላይ ብልሽት ሲያጋጥም ጉዳዩን ከሚመለከተው የቴክኒክ ባለሙያ ጋር በመነጋገር በአካባቢው በሚገኝ ጋራዥ መለስተኛ ጥገና እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ አሽከርካሪው ያስጠገነበትን ሂሳብ ለትራንስፖርትና ጥገና ቡድን በማቅረብ የጥገና ክፍል ኃላፊው ስለ ወጪው ትክክለኛነት እንዲያረጋግጥ በማድረግ እንዲወራረድባቸው ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ተሽከርካሪዎች በብልሽት ከከተማ ዉጭ በሚቆሙበት ወቅት ለጥበቃ የተከፈለዉ ክፍያ የፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት በሚያዘጋጀዉ ሰነድ የክፍያዉ ትክክለኛነት ተረጋግጦ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

9.8. የጭነት ተሽከርካሪዎች ለመስክ ስራ በሚሄዱበት ወቅት ለመክና ማሳደሪያ ጥበቃ የፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት በሚያዘጋጀዉ ሰነድ ወይም በሌላ ህጋዊ ሰነድ የሚወራረድ ይሆናል፡፡

9.9. የኤጀንሲዉ መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች እና የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ግዥ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የግዥ ጥያቄ በጀትን መሰረት በማድረግ በቴክኒክ ክፍል በኩል ለትራንስፖርትና ጥገና ቡድን ያቀርባል፡፡

## 10. **የተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች**

10.1. የመንገድ ሥነ ሥርዓት ደንብን በመተላለፍ በተፈፀመ ስህተት ቅጣቱን ሆን ብሎ ባለመፈፀም በሌላ ጊዜ ተሽከርካሪው እንዲያዝ ያደረገ አሽከርካሪ ሥራን፣ ተሳፋሪን እና ተሽከርካሪን በሥራ ላይ በማጉላላት ጥፋት የፈፀመ በመሆኑ በዲሲኘሊን ጉድለት በመ/ቤቱ የዲሲኘሊን አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ይጠየቃል፡፡

10.2. በተሽከርካሪዎች ላይ የአካል ስርቆት በሚያጋጥምበት ጊዜ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም ጥፋቱ ለጥንቃቄ ጉድለት የጠፋ ከሆነ ተሽከርካሪው የያዘው ሹፌር እንዲተካው ይደረጋል፤

10.3. በተሽከርካሪው ላይ የመገልበጥ ሆኔ የግጭት አደጋ ሲደርስ በተመደበዉ የመ/ቤቱ አሽከርካሪ ከሆነ ፡-

ሀ. አደጋዉ ከአሽከርካሪዉ ጥንቃቄ ጉድለት ስመሁኑ በትራፊክ ምርመራ ሪፖርት ከተደረገ

ለ. በንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በኩል ኮሚቴ በማዋቀር ጉዳዩ ተጣርቶ አሽከርካሪዉ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ አሽከርካሪዉ የመድን መግቢያ መነሻ /Excess/ ክፍያ እንደተሽከርካሪው ዓይነት እንደሚከተለዉ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

10.3.1. አደጋውን ያደረሰው አውቶሞቢል ተሽከርካሪ ከሆነ የመድን ሊከሰስ ከሚጠይቀው ክፍያ 50% እና የትራንስፖርት ህግ ደንብ መተላለፍ ክፍያን ጨምሮ ይከፍላል፡፡

10.3.2. አደጋው የደረሰው በመስክ ተሽከርካሪ HZJ-76, HZJ-78, HZJ-79, HZJ-105, Prado, V8 ሚኒባስ ወ.ዘ.ተ. ከሆነ የመድን ሊከሰስ ከሚጠይቀው ክፍያ 40% እና የትራንስፖርት ህግ ደንብ መተላለፍ ክፍያ ጨምሮ አሽከርካሪው ይከፍላል፡፡

10.3.3. አደጋው የደረሰው በጭነት አሽከርካሪዎች IVECO-380 Actors 380, Mersedise 1928, 1017 እና ISUZU FSR ወ.ዘ.ተ የመድን ሊከሰስ ከሚጠየቀው ክፍያ 30% እና የትራንስፖርት ህግ ደንብ መተላለፍ ክፍያ ጨምሮ አሽከርካሪው ይከፍላል፡፡

10.3.4. የኢጀንሲው ንብረት ከሆነው ተሽከርካሪ ላይ ዋጋቸው ከብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ የሚበልጥ የተሽከርካሪ እቃ ቢጠፋ በአንሹራንስ ድርጅት እንዲሸፈን የሚደረግ ሲሆን ተሽከርካሪውን የያዘው ሹፌር ወይም የስራ ኃላፊ የኢከሰስ ክፍያ 50% እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

10.3.5. ለዉቶሞቢል የሆኑ ተሽከርካሪዎች የጎን ማሳያ መስታወት፣ ፍሬቻ፣ የዝናብ መጥረጊያ ወዘተ... ሲሰርቁ ለሽከርካሪው የተሰረቀውን እቃ ዋጋ 30% ይከፍላል፤

10.3.6. የመስክና የተለያዩ የጭነት ተሽከርካሪዎች የጎን ማሳያ መስታወት፣ ዝናብ መጥረጊያ፣ ፍሬሎክ ወዘተ... ሲሰረቁ ለሽከርካሪው የተሰረቁትን እቃ ዋጋ 20% ይከፍላል፤

10.3.7. በተሽከርካሪ ለካል ላይ ስርቆት ሲከናወን እና የተሰረቀው እቃ ዋጋ መድን በተገባለት ሊከሰስ ክፍያ ዋጋ በ3 /ሶስት/ እጥፍ ከፍ ያለ ከሆነ በመድን ዋስትና ሽፋን እንዲተካ ይደረጋል፤ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሽከርካሪዉ የሊከሰስ ክፍያዉን ለመ/ቤቱ እንድከፍል ይደረጋል፡፡

10.3.8. ተሽከርካሪው ለደጋ ደርሶበት ሳያሳውቅ በሚመለከተው ለካል ቁጥጥር ተደርጎ ሲገኝ ለሽከርካሪው የጥገና ዋጋውን ይከፍላል፤

10.3.9. መንጃ ፈቃድ ሳያሳድስ ቀርቶ ተሽከርካሪ ጉዳት ቢያደርስና የመድን ሽፋን ባያገኝ በጉዳቱ ለሚጠየቀው ክፍያ መ/ቤቱ የሚሸፍን ሆኖ በመ/ቤቱ የዲሲኘሊን መመሪያ እርምጃ ለፈጻጸም የሚጠየቅ ይሆናል፤

10.3.10. በመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ላይ በለያያዝ እና በለጠቃቀም ጉድለት ችግር መድረሱን በቴክኒክ ክፍል ለትራንስፖርት ክፍል ጥገና ቡድን ሪፖርት ሲቀርብ ለጥገና የወጣውን ወጪ በመ/ቤተቱ የሚሸፍን ሆኖ ለሽከርካሪዉ በዲሲኘሊን እርምጃ ለፈጻጸም መመሪያ መሠረት የሚጠየቅ ይሆናል ፡፡

10.3.11. በማስተባበሪያ ጽ/ቤት ስር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ከማስተባባሪያ ጽ/ት የስራ ክልል ዉጭ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የንብረት ለስተዳደሩና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

10.3.12.

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 11. የትራንስፖርት ስምሪት ለሰጣጥ

11.1. በለዲስ ለበባ ከተማ ውስጥ ለሚጠየቀዉ የስምሪት ለገልግሎት ስምሪት በትራንስፖርትና ጥገና ሶፊሰር ይከናወናል

11.2. በንዑስ አንቀፅ 12.1 ከተገለጸዉ ቦታዎች ውጪ ወይም ለመስክ ለሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች ለዝህ ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ ተጠቃሚው ክፍል ጥያቄ፣ ሲያቀርብ በትራንስፖርትና ጥገና ቡድን ሲፈቀድ ትራንስፖርትና ጥገና ኦፊሰር ስምሪት ይሰጣል

11.3. በውስጥ ለሚጠየቁ ተሽከርካሪዎች በንብረት አስተዳደት ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ሲፈቀድ ብቻ ተግባራዊ ይሆናል፤

## 12. የኤጀንሲዉ የስራ ክፍሎች ሚና

12.1. የፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት በዝህ መመሪያ የተገለጹ ቅጣቶች ወይም ተተኪ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ከትራንስፖርትና ጥገና ቡድን በሚቀርበዉ ማስረጃ መሰረት ክፍያዉን ያስፈጽማል።

12.2. የሰዉ ሀብት ልማትና አመራር ዳይሬክቶሬት በዝህ መመሪያ ዉስጥ የተቀመጡ የዲሲፕሊን ጉዳዮች ከንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሚያቀርበዉ ማስረጃ አስፈላግዉን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል።

## 13. የተሻሩ መመሪያዎች

የትራንስፖርት አጠቃቀምና አስተዳደር አፈፃፀም መመሪያ አስመልክቶ ከዚህ በፊት በኤጀንሲዉ ሲሰራባቸው የነበሩ መመሪያዎች ሁሉ በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

## 14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ከተፈረመበት ጊዜ ጥር 08/2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

## የጥገና አገልግሎት ቀጠሮ መጠየቂያ

የተሽከርካሪው ዓይነት______________________________ የቻንሲ ቁጥር______________________

የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር_________________ ሞዴል____________________________________________

የጥገናው ዓይነት_______________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________________

የጠየቀው የትራንስፖርትና ጥገና ኦፊሰር ስምና ፊርማ_____________________________

ለጥገና ቀጠሮ የተያዘለት ቀን_______________ቀጠሮ የሰጠዉ

የጥገና ክፍል ኃላፊ ስምና ፊርማ__________________________

---

## የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

## በከተማ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት መጠየቂያ ፎርም

የባለጉዳዩ ስም____________________________________ለግል ጉዳይ________ለመ/ቤቱ ስራ-ክፍሉ___

_____________________________የሚሄድበት ቦታ ሐየጠየቀበት አገልግሎት________________

የአገልግሎት ጠያቂ ፊርማ__________________ የቅርብ ኃላፊ ስምና ፊርማ________________

ጥያቄ የቀረበበት ቀን_ሰዓት_________________አገልግሎት የተሰጠበት ቀን__________

ሰዓት_________________ የሰሌዳ ቁጥር_______________የአሽከርካሪው ስም__________________________

የተመለሰበት ሰዓት_________________ የፈቃጁ ፊርማ_____________________

---

## የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉይ ኤጀንሲ

## የጭነት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ

ቀን__________________

1. ጥያቄዉን ያቀረበዉ ቡድን________________
2. የሚጓጓዘዉ ዕቃ ዓይነት____________ዕቃዉ የሚጓጓዝበትቦታ የጭነት መጠን__________ _______ኩንታልሜትሪክ ቶን_______________ሊትር_______________
3. የሚጓጓዝበት ቀን___________________
4. ጥያቄዉን ያቀረበዉ ሠራተኛ ስም_________________ፊርማ_______________ቀን__________
5. ጥያቀዉን ያጸደቀዉ ስም_________________ፊርማ_______________ቀን_________________

**በትራንስፖርትና ስምሪት የሚሞላ**

1. የተመደበዉ ተሽከርካሪ ታርጋ ቁጥር _____________የአሽከርካሪዉ ስም_________________
2. ተሽከርካሪዉ ለመጫን ዝግጁ የሚሆንበት ቀን___________________ሰዓት________________
3. ጠያቂዉ ክፍል ለጠየቀበት ተሽከርካሪ ማሰማራት ይቻላል ☐ አይቻልም ☐ ማሰማራት የማይቻል ከሆነ ምክንያትና ተለዋጭ ቀጠሮ_________________
4. ተጨማሪ አስተያየት________________

_____________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________

የትራንስፖርትና ጥገና ቡድን

ስም ________________ ፊሪማ_________________

ማሳሰቢያ፡- የጭነት ተሽከርካሪ አገልግሎት ጥያቄ እቃዉ እንድጓጓዝ ከተፈቀደበት ዕለት ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡